## ሱባዔ ከጎበዝ አለቆች ጉባዔ(ከማህበረ «ቅዱሳን»)

በአትላንታ የሰዓሊተ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን የህጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ አመራር ከሚቀበሉት አብያተ ክርስቲያናት በመጀመሪያ ተርታ ከሚቀመጡት አንዷ ነች። ቤተክርስቲያኗ ለአትላንታና አካባቢው ለሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን መንፈሳዊ አገልግሎቶችን በመስጠት በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ቀዳሚና የላቀ ድርሻ አላት። ከዚህም በላይ በዓለም ዓቀፋዊ የኦርቶዶክስ የስነ ህንጻ ዲዛይን ስርዓት መሰረት ከአምስት ዓመታት በፊት በህጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ በተመረቀና በተባረከ ህንጻ ቤተክርስቲያን አገልግሎት መስጠት ጀምራለች። እንደዚሁም ከ20 ዓመታት በላይ በፍጹም አባታዊ ፍቅርና ትዕግስት በህዝበ ክርስቲያኑ ያገለግሉት አባት መልካም እረኝነታቸው ታይቶና ተመስክሮም ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለጂዮርጂያ፤ ቴነሲና ለኖርዝ ካሮላይና ሊቀ ጳጳስ አድርጎ ሰለሾማቸው የአትላንታ ቅድስት ማርያም የመንበረ ጵጵስና ቦታ ለመሆንም በቅታለች። ይህችን ቤተክርስቲያን በአትላንታና አካባቢው በሚገኙ ምዕመናን ተወዳጅነት ያተረፈችው ኢትዮጲያዊት ቤተክርስቲያን ስለሆነች ምዕመኖቿን የእግዚአብሔር ቃል ከማስተማር ጋር ኢቲዮጵዮጲያዊ ማንነታቸው በልባቸው ጽላት እንዲቀረጽ ስለምትተጋ ነው። የመልካም ነገር ሁሉ ባላጋራ የሆነው ዲያብሎስ ጦሩን ሰብቆ በዚህች ታሪካዊት ቤተክርስቲያን ከተነሳሳ ሰነባብቷል። ቅዱስ መጽሐፍ «ባላጋራችሁ ዲያብሉስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራል» 1 ጴጥ5፤8 እንዳለው የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክና ሃይማኖት ባላጋራ የሆነው ወያኔ የቤተክርስቲናያችንን አንድነት ህልውና እየተፈታተነ ይገኛል። በስደት የሚገኘውን ህዝብ ለመከፋፈል ወያኔ ከነደፋቸው እቅዱች አንዱ አብያተ ክርስቲያናትን ጨምሮ በውጭ አገር የሚገኙ የተለያዩ የኢትዮጵያውያን ተቋማት ውስጥ የራሱን ካድሬዎች ሰርጎ ማስገባት ነው። ይህንን የወያኔ ተሞክሮ ለማስታወስ በዋልድባ ገዳም ካድሬዎቹን መነኩሴ እያሰመሰለ ሲያስገባ እንደነበረ ከወያኔ መስራች አባል የሆኑት የዶ/ር አረጋዊ መጽሐፍ ልብ ይሏል።በዚህ ወቅት በሰደቱ ዓለም ከየትትኛውም የኢትዮጲያውያን ተቋማት ብዙ ህዝብ ያሰባሰበው የህጋዊው የኢኦተቤክ መሆኑ ስለሚታወቅ በቅርቡ ወያኔ 7 የሚሆኑ አፈ ጮሌ መነኮሳት ወደ ሀገረ አሜሪካ እንደላከ መረጃዎች ያሳያሉ። በመሆኑም በአትላንታ የሰዓሊተ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የዚህ እጣ ፈንታ ደርሷት ተኩላው የበግ ለምድ ለብሶ ገብቶ መንጋውን በማተራመስ ላይ ይገኛል። ዲያብሎስ መንጋን ለመበተን ዓይነተኛ ስልቱ እረኛን መምታታት በመሆኑ ተኩላው እኩይ ስራውን የጀመረው የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ በመፈታተንና በመተናኮል ከምእመናንና ከቦርድ አባላት ለመለያየት በመሞከር ነው።

አንድ ክርስቲያን ህይወቱን ለመፈተሽ ሲያቅድ በእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ መሆኑን የቤተክርስቲናያችን አስተምህሮ ያስረዳናል። ሆኖም የቀድሞ የሰዓሊተ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የአስተዳደር ቦርድ አስተዳዳሪ ብሎ የሾማቸው መነኩሴ ከወቅቱ ቦርድ ጋር የ12 ሰዓታት ስብሰባ ካካሄዱ በኋላ በውሳኔው ያልተደሱት አባ ኃ/ሚካኤል በማግስቱ ክርስቲያናዊ ሕይወቴን ልፈትሽ(ሱባኤ ልግባ) ብለው በአውደ ምህረት ላይ ካወጁ በኋላ በምስል በተደገፈ ማስረጃ በጎበዝ አለቆች ጉባኤ ወይንም ራሱን ማህበረ «ቅዱሳን» እያለ የሚጠራው 16ኛው ጉባኤ ላይ መገኘታቸው ምእመኑን አስደንግጧል። የአባቶች ከሳሽ ማህበረ «ቅዱሳን}፣ ከወያኔ ጋር የጥቅም ጋብቻ የፈጸመው ማህበረ «ቅዱሳን»፣ በስደት ላይ የሚገኙትን አባቶችን በማሳደድ የወያኔ ተልእኮ የፈጸመው ማህበረ «ቅዱሳን» ጋር እንዴት አድርገው ይሆን አባ ህይወታችውን የሚፈትሹት? ምናልባትም መንፈስ ቅዱስ በመንጋው ላይ የሾማቸው የብጹዕ አቡነ ያዕቆብን ሀገረ ስብከት ማተራመስ፣ እርሳቸውን ማሳደድ፤ ምእመናኑን መከፋፋል ብሎም ቤተክርስቲያኗን ለወያኔው አሳልፎ የመስጠት አጀንዳ መቅረጽ? አባ ኃ/ሚካኤል በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት ቆመው ራሳቸው ላይ ሱባኤ አውጀው ሄደው ነገር ግን ቺካጎ ከተማ ከሜይ 24-26 የሚኔሶታውን መድህኔ አለም ቤ/ክን ከፍለው ወደ ወያኔው ሲኖዶስ የወሰዱት አቡነ ዘካርያስ በሚመሩት የማህበረ «ቅዱሳን» ስብሰባ ላይ መገኘታቸውን የሚያሳየው የምስል ማስረጃ ፤ በእውነት አደባባይ ላይ የሃሰት

መልእክት አባ ኃይለሚካኤል ለምእመናኑ አስተላልፈዋል የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሳል። ይሄ ደግሞ የአብዛኛው ምእመናን እምነት ነው በመሆኑ ወደፊት አባ አውደ ምህረት(የምህረት/የእውነት አደባባይ) ላይ የሚያስተላልፉትን መልእክታት አንደምንና እንዴት እንደሚወስዱት አጠያያቂ ሆኗል።

**<u>አባ ኃይለሚካኤልን ያላስደሰተው የስብሰባ ውሳኔ ምን ነበር?</u>**

ነገሩ እንደዚህ ነው። የኖርዝ ካሮሊና ቅድስት ስላሴ ቤ/ክ ለብዙ ዓመታት በገለልተኝነት ከቆየች በኋላ ገዳማዊው አባት በአባ ገብረ ማርያም መንፈሳዊ አመራርና ትምህርት ህጋዊውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቦርድ ቅዱስ ሲኖዶስ ለመቀላቀል በቅታለች። በመሆኑም የቤተክርስቲያኗ ቦርድ ሊቀ መንበር ይህንን መልካም ዜና በኢሳት ሬድዮ በተለያዩ የዜና ማሰራጫ አገልግሎት ቀርበው ማብሰራቸው የሚታወስ ነው። ቤተክርስቲያኗ ቋሚ ካህን አጥቷ በተቸገረበችበት ሰዓት አባ ገብረማርያም በቦርድ ሊቀ መንበር በሆነው ዶ.ር ሰለሞን ጉግሳ ጉትጎታ በብጹዕ አቡነ ያዕቆብ ፈቃድ ወደ ቻርለት ሄዱ። ቀድመው ከነበሩበት ስፍራ የጀመሩትን የ Immigration Process አቋርጠው ኖርዝ ካሮሊና አገልግሎት ይጀምሩና እኛ እናስፈጸምላችኋለን ብለው ቃል ኪዳን ተገብቶላቸው ከሄዱ በኋላ የቦርዱ ስራ ዘመን ወደ ማለቁ ግድም የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም አባ ገብረ ማርያም እንቅፋት ይሆኑብኛል በሚል ስጋት ዶ/ሩ ለ Immigration የገባውን ማመልከቻ በደብዳቤ እንዲቋረጥ አድርጎ በመጨረሻም ካህኑን ከአግልግሎት እንዲሰናበቱ አድርጓል። አባ ገ/ማርያም ከመንፈሳዊ ትሩፋታቸው በተጨማሪ በአገራችን ኢትዮጵያ በዋልድባ ገዳማትና አድባራት ላይ በተደረገው የጥፋት ዘመቻን አስመልክቶ ኢትዮጵያውያንን ክርስቲያኖችን ከተለያዩ አድባራት በማስተባበር ከፍተኛ ተቃውሞ ድምጽ በማሰማት ለሃይማኖትና ለሀገር ፍቅር በቆራጥነት መቆምን በተግባር ያስተማሩ፤ ትግሉንም በማስተባበር እስከ ዋሽንግተን ዲሲ ድረስ በመሄድ በግንባር ቀደምትነት በማስተጋባት አርአያነታቸውን ያስመሰከሩ መንፈሳዊ አርበኛ ናቸው። በደሉን የከፋና አስገራሚ የሚያደርገው ደግሞ የዚህ በደል ምንጭ አካል ዘረኛው የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈጽመውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እፋለማለሁ የሚልና አልፎ ተርፎ ባለፉት ወራት በሳውዲ አረብያ መንግስት የግፍ ጽዋ ተቋድሰው ወደ ሃገር የተመለሱትን ወገኖች ለመርዳት ከተቋቋመውና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች በሆነው አርቲስት ታማኝ በየነ የሚመራው የ (Global Alliance) አባል የሆነው ግለሰብ እንደዚሁም በኖርዝ ካሮሊና የቅድስት ስላሴ ቦርድ ሊቀመንበር የሆነው ዶክተር ሰለሞን መሆኑ ነው። የዶክተር ሰለሞን እጅግ ጭካኔ የተሞላበትን አድራጎት እርስ በርሳችው የሚጣረሱ ስብዕና እንዳለው ፍንትው አንድርጎ የሚያሳይ ነው በተጨማሪም ማህበረሳባችን እንደነዚህ ዓይነት የትግሉ እንክድርዳዶችን አንጓሎ ከመሃሉ ነጥሎ እንዲያወጣቸው ግድ ይላል። የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች ይሉሃል የወንድማችን ዶ/ር ሰለሞን አድራጎት ነው።የዶ/ር ሶሎሞን አስተዳደር ቦርድ ኢፍትሐዊና ኢሰብዓዊ እርምጃና ምእመናን በመቃወማችው በቤተክርስቲያን ውስጥ አምባጓሮና መካፋፈል ፈጠረ። ምንም እንኳን የቤተክርስቲያኑ አባላት በቤተክርስቲያኗ ሰላም ለማምጣት ጥረታቸውን ቢቀጥሉም ነገሩን መፍታት ስላልቻሉ የሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ብጹዕ አቡነ ያዕቆብ ሄደው አባታዊ ምክር እና የሽምግልና በር ከፍተው እንዲያስማሙ ምዕመናንና እና አባ ገ/ማርያም ጥያቄ አቀረቡ። ነገር ግን የቤተክርስቲያኑ ቦርድ ሊቀ ጳጳሱ ወደ ቻርለት እንዳይሄዱ የማማስፈራራት ሙከራ ቢያደርጉም ከሀዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ የተሰጣችው ስማያዊ የቤተክርስቲያን አደራ ግድ ስላላችው እንዲጠብቁት ለተሾሙበት መንጋ ሰላም ለማውረድ ብጹዕነታችው ወደ ሻርለት ተጓዙ። ወደሻርለት እንደደረሱም ዶክተር ሰለሞን ሊቀ ጳጳሱ ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ የፖሊስ ማዘዣ ወረቀት ይዞ ስለጠበቃቸው በደጃፍ ቆመው አስቀድሰው ከጨረሱ በኋላ ህዝበ ክርስቲያኑን ማጽናናት ችለዋል። የሚገርመው ነገር ከውስጥ በቅዳሴው ላይ የብጹእ አቡነ ያዕቆብ ስም እየተጠራ እሳቸውን ግን ገብተው ጸሎት ማድረግ እንደዚሁም ምዕመናኑን መባረክ ተከልክለዋል። በተጨማሪም የብጹእ አቡነ ያዕቆብን በደጃፍ መቆም ያዩ ምዕመናን በሙሉ አብረው ውጭ ከብጹዕነታቸው ጋር በመቆም አሰቀድሰዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ዶ/ር ሰለሞን በብጹእ አቡነ ያዕቆብ መንፈሳዊ

አመራር ስር ያሉትን አባ ኃይለሚካኤልን ወደ ቤተክርስቲያኑ ይጋብዛል። ወደ አትላንታ ሲመለሱም የቦርድ አባላት፣ ካህናትና የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ባካሄዱት ስብሰባ አባ ኃ/ሚካኤል የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ሳያሳውቁና ሳያስፈቅዱ መሄዳቸው የኦርቶዶስሳዊት ቤተ ክርስቲያን ስርዓት ያፋለሰ እንደሆነ ሲነገራቸው ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ጠይቀዋል። በተጨማሪም በቤተክርስያናችን ቀኖና መተዳደሪያ መሰረት ማንኛውንም መንፈሳዊ መመሪያ ከብጹነታቸው እንዲቀበሉ ቦርዱ በአንክሮ ነግሯቸው እርሷቸውም መመሪያውን ተቀብያለሁ ብለው የብጹዕነታቸውን ጉልበት ስመው ከ10 ሰዓታት በኃላ ስብሰባው ተፈጽሟል። በስብሰባው ውጤት ልባቸው ያልተደሰተው አባ ኃ/ሚካኤል በማግስቱ ከላይ በርእሱ የተጠቀሰውን የራሴን ልፈትሽ(ሱባኤ) ንግግር አውደ ምህረት ላይ አድርገው ነገር ግን በማህበረ «ቅዱሳን» ስብሰባ ላይ ነበር የተገኙት። በአንፃሩ ቦርዱ ተከስቶ የነበረው ችግር ተፈታ ሰይጣን ድል ተመታ የሚል ሪፖርት ለህዝብ አውደ ምህረት ላይ በማቅረቡ ህዝብ በዕልልታና በጭብጨባ ተቀብሎታል።

<u>አጠቃላይ አስቸኳይ የምዕመናን ስብሰባ</u>

ሰይጣን ድል ተመታ ብሎ እፎይ ብሎ ሊቀመጥ የታዘጋጀው ምእመን አባ ከእግዚአብሔር ቃል ራሳቸውን ፈትሸው ምንም እንኳን ጸጋቸው ዜማ(መሪጌትነት/ደብተራነት) ቢሆንም እኛንም በቃለ ወንጌል ያንጹናል የቤተክርስቲያናችንን የህንጻ እዳ ለማቃለል በምናደርገው ርብርቦሽ ያግዙናል ብለን ስንጠብቅ ራሱን ማህበረ «ቅዱሳን» እያለ ከሚጠራው የጎበዝ አለቆች ጋር ስብሰባ ተቀምጠው ሲመክሩ የሚያሳይ ፎቶግራፍ ለምእመኑ ደረሰን። ይባስ ብሎ ስብሰባው የሚመሩት የሚኒሶታ መድኃኔ ዓለም ቤ/ክ ለመከፈል ምክንያት ከሆኑት ጋር በመሆኑ የአትላንታ ሰዓሊተ ማርያም ቤተክርስቲያን ምእመናንን ያስደመመ ነበር። በተጨማሪም በሱባኤ ምክንያት ፈቃድ ወስደው በስደት ላይ የሚገኘውን ህጋዊ ሲኖዶስ ወያኔ ጥግ አድርጎ ሲያሳድድ ከነበረው የወያኔ መንፈሳዊ ክንፍ ቡድን ከሆነው ከማህበረ ቅዱሳን ጋራ መሳበሰባቸው በምእመናን ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤና ግርግርን ጫረ። እንደሚታወቀው ማህበረ «ቅዱሳን» ከወያኔ ጋራ የጥቅም ጋብቻ ፈጽመው በጥቅም ጉዳይ እንደተጣሉ ይታወቃል። የዓላማ አንድነት ግን የጥቅም ግጭት በመኃላቸው እንደተፈጠረ አንባቢ ልብ ይበል! ድሮም ሌባ ሲካፈል እንጂ ሲሰርቅ አይጣላ ይባል ነበረ።ሌላው የዚህ እኩይ ማኅበር መገለጫው ሁሉም ቦታ አለሁበት ማለቱ ነው። የወያኔ መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ ተቋዋሚውን ክፍል «በመንግስታችሁ አስቡኝ» የሚሉ ጎዶች ናቸው። አባ ኃ/ሚካኤል ከስብሰባው እንደተመለሱ እንደገና የሁለት ወር እረፍት ጠይቀው ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ። ምእመናንን፣መዘምራንና የቦርድ አባላት የከፋፈለው የአባ ኃ/ሚካኤል ስውር አጀንዳ ያሳሰባቸው የቤተክርስቲያኑ አባላት አስቸካይ ጠቅላላ ስብሰባ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት እንዲካዳሄድ ጠይቀው በቦርዱ አማካይነት ሰብሰባው ተካሄደ።

አጠቃላይ የአባላት ስብሰባ ትእይንት ጉደኛ ነበር። በጠቅላላው ቤተክርስቲያኗ ላለፉት ሁለት ዓመታት የታመሰችበት ምክንያት ነጥሮ የወጣበት እርሱም በብርሃን ፍጥነት የቀድሞ ቦርድ አስተዳዳሪ ብሎ የሾማቸው አባ ኃ/ሚካኤል እንደሆኑ ታውቋል። እንደዚሁም በሚያስደንቅ ሁኔታ ወያኔ በግልጽ በቤተክርስቲያኑ አባላት የተወገዘበት በአንጻሩ ደግሞ የስርዓቱ ተጠቃሚዎችና የትግል እንክርዳዶች በሚያሳዝን ሁኔታ የታዩበት ነበር። በዚህ ስብሰባ ላይ የተንጸባረቁት አንኳር ሃሳቦች እንደሚከተሉት ናቸው። የቤክርሲቲያኑ መተዳደሪያ እንዲከበር፣ በመንፈሳዊ አስተዳደር ውስጥ ቦርዱ ጣልቃ እንዳይገባ፣ የቤተክርስቲያኒቷ ቀኖና መሰረት በሚያዘው መሰረት በማንኛውም መንፈሳዊ ጉዳይ ላይ መመሪያ የሚሰጡት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ እንደሆኑና ከህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጥላ ስር ካፈነገጡ ካሉ አብያተ ክርስቲያናትና እንደ ማህበረ ቅዱሳን ካሉ አካላት ዘንድ ሄዶ ማገልገል ይቻል እንደሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ በጽሁፍ እንዲጠየቅ የተወሰነ ሲሆን በመጨረሻም ሁለት ዓመት ብቻ ላገለገሉት አባ ኃ/ሚካኤል በመጀመሪያ ለ15 ቀን ቀጥሎም ለሁለት ወር በቅድሚያ ደሞዛቸውን ከፍሎ ሊያውም ቤተክርስቲያና በየዕለቱ በምትቀድስበት በፍልሰታ ፆም ወቅት ዕረፍት መፍቀዱ ይህም ያለ ሊቀ ጳጳሱ ፍቃድ በመሆኑ ቦርዱ

ተተችቶ ይህንን አሰራር እንዲያርምና ወደፊት የዕረፍት አሰጣጥን አስመልክቶ ቋሚ ደንብ እንዲወጣ ተጠይቋል። በሌላ በኩል ደግሞ የቀድሞ ቦርድ የስራ አመራር የከፈሉት የጊዜና የጉልበት መስዋእትነት ጉባኤ አመስግኖ አብዛኞቹ የአመራር አባላት ደግሞ ደጋግመው በመመረጣቸው የአሰራር ዝርክርነትና ዘባቶሎነት ስለታየበት የቁጥጥር ኮሚቴው የኦዲት ዘገባውን እንዲያቀርብ አስረግጦ ተወያይቷል። የሰብሰባውን አመራርና አካሄድ አሰመልክቶ፤ እስከዚያ ቀን ከተካሄዱት ጉባኤዎች የአባላት ብዛት ከምንም ግዜም በላይ የታየበት ቢሆንም ጥቂት የቀድሞ ቦርድ አባላት ኮረም አይሞላም ብለው ስብሰባው እንዳይዳካሄድ የተወራጨበት ነበር። የስብሰባው መሪ ወያኔ የሚጠየፉ ታላቅ ሰው ቢሆኑም ከቀድሞው ቦርድ አባላት ያላቸው የቆየ ወዳጅነት ቢጎትታቻቸውም ከሞላ ጎደል ስብሰባውን ጥሩ መርተውቷል። የጤና ባለሞያው ምክትል ሊቀመንበሩ ግን የወያኔ ስርዓት ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚያቁ አባላት «አይ 140 ካሬ ሜትር» ጉድ ሰራች ብለው ታዝበዋል። በዚህ ስብሰባ ላይ የነበረው የሴቶች እህቶቻችን የተነቃቃ ተሳትፎ እንደዚሁም የወሰዱት ቆራጥ አቋም ለአገር ወዳዶች ይበል ያስባለ ሲሆን ለሎች ደግሞ የእግር እሳት ነበር። ስለሆነም አንዱ ጀቢራ ተነስቶ «ሴቶችን አደብ ግዙ ነገ ደግሞ ታቦት እንሸከም እንዳትሉ እናንተ አይደላችሁም እንዴ አባ ኃ/ሚካኤል ሲመጡ መኪና ያስገዛችሁት» በማለት ወርፎአቸዋል። ይሄ ጀቢራ ያልገባው ነገር ቢኖር በአዲስ ኪዳን የመጀመሪዋ ታቦትና ቤተ መቅደስ  ሴት የሆነችው እናታችን ቅድስት ማርያም መሆኗን ነው። በአዲስ ኪዳን ሴቶች እንዲዚሁም ክርስቲያች በሙሉ የእግዚአሔር ቤተመቅደስና ህያው ታቦታት ናችው። ለነገሩ ይህ ግለሰብ በቅዳሴና በትምህርት ሰዓት ዳዊት በመድገም የግል ጸሎትን ሲያደርግ ተሰተውሏል። በመሠረቱ የእሁድ ስርዓተ ቅዳሴ እኮ የማኅበር ጸሎት ነው። በማኅበር ጸሎት ወቅት የግል ጸሎት ማድረስ በጋቢ ላይ ነጠላ እንደመደረብ ነው። ለወንድማችን ማስተዋልን ይስጥልን። ሌሳው ትዕይንት አንዲት የጋብቻዋ በዓል ቀን በአባ ኃ/ሚካኤል የደረሰባትን የአስተዳደር በደል ለመናገር ስትሞክር የደረሰባትን ወከባ የማይታለፍ  ነው። ልጅቷ ወከባውን ተቋቁማ የማኅበረ ቅዱሳን ዘማሪዎችን እንድትጠራ የደራሰባትን ግፊት እንደዚሁም የጋብቻዋ ዕለት የሙሽራ ልብሷ ባህላዊ ስላልሆነ በመቀስ መቁረጥ ነበር ብለው መድረክ ላይ  በመናገራቸው የስርጓን ደስታ ወደ ሃዘን እንደለወጡት ተናግራለች። ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው አንድ አፍቃሪ ማህበረ ቅዱሳን የሆነ ወጣት የተናገረው አሰናካይ ንግግር ነው። ይህ ወጣት በአትላንታ የኢትዮጲያውያን ማህረሰብ ሁለገብ ተሳትፎ ያለው ነው ማለትም በኮሚኔቲ፣በቤተክርስቲያን፤በሬድዮ እንዲሁም በወያኔ መንግስት ተቃዋሚው ክፍል ወዘተርፈ። ታዲያ በዚህ ስብሰባ ላይ ሃይማኖትን ከፖሊቲካ እንድንለይ ካሳሰበን በኋላ ህጋዊው ፓትርያርክና ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተለያዩ እንደሆኑ ደሰኮረ፥ ከመረቁ ስጡኝ ስጋው ይቅርብኝ እንደማለት ነው። ወያኔ የኦርቶዶክስ ቤ/ክ ላይ የከፈተውን ጦርነትና እያደረሰ ያለውን ጥፋት እኛ አርቶዶክሳውያን ዝም ብለን እንዳይ ይሆን? ደግሞስ ኢትዮጵያ ያሉትን ጳትርያርክ አንቀበልም ግን ሲኖዶሱን እንቀበላለን እንደሚሉት ራሳቸውን ገለልተኛ ብለው እንደሚጠሩት ዘመነኛ አብያተ ክርስቲያናት መኮኑ ይሆን? ለአትላንታ ቤ/ክ የተደገሰላት ስውሩ አጀንዳ እሱ ይሆን? የሚገርመው በዓለሙ ቋንቋ ጠቅላይ ሚኔስቴሩን አልቀበልም ግን ካቢኔዎችን እቀበለላለሁ እንደማለት ነው። የዚህ ወጣት አካሄድ በትክክል የትግሉ እንከርዳድ መሆኑን አንጸባራቂ ነው። ስለሆነም ወጣት ስለሆነ ተመክሮ እንዲመለስ ማረግ በትግሉ ዓለም ተሞክሮ ካላቸው ሰዎች ይጠበቃል ካልሆነም ከትግሉ ሜዳ ሳይረፍድ ማንጓለል ነው።

<u>ዘባተሎውና ዝርክርኩ የአስተዳደርና ቦርድና አባ ኃይለሚካኤል</u>

ከላይ እንደጠቀሰው የቀድሞ ቦርድ አባላት የአሰራር ዝርክርነት እንዳሳዩ ጉባኤው ተመልክቷል። እንደሚታወቀው የፈቃደኝነት ስራ ከግል ስራ፣ከቤተስብና ከዕረፍት ጊኤ መስዋዕት ተደርጎ የሚከናወን ስለሆነ ሊከበሩና ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። በአንፃሩ እንደ ማንኛውም አትራፊ ያልሆነ ድርጅት አገልጋይ መልካም አስተዳደር አስመልክቶ ከተጠያቂነት አያልፉም። የተወሰኑት አራቱ የቀድሞ ቦርድ አባላት በብዛት ደጋግመው በመመረጣቸው ምክንያት የአሰራር ዝርክርነትና

እናውቀዋለን ዓይነት ግድ የሌሽነት ዓይነት አሰራር የታየባችው። የሚገርመው ሊቀመንበር፣ምክትል ሊቀመንበር፣ጸሃፊና የህዝብ ግንኙነት የነበሩት ተመልሰው ያቺኑ ቦታ ነው የሚፈልጓት።ቤተክርስቲያኗን በማተራመስ ላይ የሚገኙት አባ ኃ/ሚካኤልን ያስመጡና አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ከፍተኛ ርብርቦሽ አድርገዋል። ስለሆነም ለዚህ ሁሉ ትርምስ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።በመሆኑም የሚቀጥለውን ምርጫ ሲመጣ ዳግም ተመልሰው የተለመደ ቦታቸውን ይዘው የአባ ኃ/ሚካኤል አጀንዳ በማስፈጸም ምእመኑን ለማተራመስ እየጠበቁ ስለሆነ ምእመኑ የቤተክርስቲያኑን አንድነት የመጠበቅ ሃላፊነቱን ሙብትና ግዴታውን ለመወጣት ከምን ጊዜውም በላይ በመምረጥና በመመረጥ የነቃ ተሳትፎ ይጠበቅበታል። እነዚህ ግለሰቦች የስብሰባውም ዕለት አባ ኃ/ሚካኤልን አትወቀሱ ዕያሉ ሲሟገቱ ተስተውሏል። ለመሆኑ አባ ኃ/ሚካኤልን ከባህሬን ሲያስመጡ በስነ ምግባር ተከሰው እንደነበር፤ ክሱ ምን እንደደረሰ ተከታተለው ነው ያመጡት? ከመጡ በኋላ ለምንድነው ሳይጠኑ ቦርዱ የስራ ዘመኑን ሳይፈጽም አጣድፎ የቤተክርስቲያኗ አስተዳዳሪ እንዲሾሙ ያደረገት?

<u>የትግሉ እንክርዳዶች</u>

በአሁኑ ሰዓት ሀገራችን ኢትዮጵያን ያጋጠማት ይሉኝታ የሌለው ዘረኛና አስከፊ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተነሳ አገዛዝ ነው። የመረረ ትግልን ለሚጠይቅ እንቅስቃሴ መለሳለስ ቦታ የለውም። ትግሉ በጦዘ ቁጥር የትግል እንክርዳዶችም ይበዛሉ ስለሆነም እነዚህን ከትግሉ ሜዳ እያንጓለሉ ወደፊት መሄዱ ብቸኛ አማራጭ ነው። በመሆኑም ህጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲሉም በሌሎች የኢትዮጵያውያን ተቋማት በውስጥ ተሰግስገው እኛ ያላቦካነው ዳቦ አይጋገርም የሚሉት እንደ ዶክተር ሶሎሞን፣ ዶክተር ነጋና ምርጫው እንደዚሁም አትላንታ አካባቢው ያሉ አክቲቪስቶች የአሰናካዩን ወጣት አካሄድ በጥንቃቄ እየተመለከቱ ራሳቸውን ከእንደነዚህ ዓይነት እንቅፋቶች ራሳቸውን ማጽዳት ይኖርባቸዋል። በመጨረሻም ሰዓሊተ ማርያም ቤ/ክን ለብዙ ዓመታት ሲያገልግል ቆይቶ ቅስና ከወያኔው ሲኖዶስ ተቀብዬ መጣሁ ያለው አገሊጋይ በዓረቡ ዓለም አሰቃቂ ድርጊት ለተፈጸመባቸው ወገኖቻችን ድምጻቸውን ለማሰማት ሰላማዊ ሰልፍ የወጡት ምእመናንን መድረክ ላይ መዝለፉ የሚታወስ ነው። አንድ መሉ ዓረፍተ ነገር እንኳን አሳክቶ የማይናገረው ግለሰብ «ክርስቲያን ወደ እግዜአብሔር ይጸልያል እንጂ ሰላማዊ ሰልፍ አይወጣም» በማለት ሲንዘባዘብ ተሰምቷል። የቤተክርስቲናኗን ታሪክ በጥልቀት ስላሳጤነው እንጂ ቤተክርስቲያናችን ለኢትዮጵያውያን ሃይማኖትን፣ ጀግንነትን፣ታሪክን፣ፊደልን፣ባህልና ኪነጥበብን ያስተማረችና ያስረከበች ስንዱ እመቤት ናት። ሌላው ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ቁርባናችንን፣ጋብቻችንና የልጆቻንን ጥምቀት ቅድስና የለውም ብሎ ያወገዘንን ከወያኔው የአባ ማትያስ ሲኖዶስ በምን ዓይነት ሁኔታ ቅስና የተቀበለው? ውግዘቱ ልክ ነው ብሎ አምና ተናዞ ነው? ከሆነስ በምን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ በመቁረብ በማቆረብና በማጥመቅ ህጋዊውን ሲኖዶስ ጥላ ስር በታቀፈች ቤተክርስቲያን የሚያገለግለው? አዲስ አበባ ቅስና የሰጡት የወያኔ ጳጳስ አሜሪካ ምን ሲያረግ እንደነበረ አውቀው ነው ቅስና የሰጡት? ሲያገልግል ከነበረበት ሀገረ ስብከት ከሊቀ ጳጳስ የምስክር ወረቀት ይዞ ሄዶ ነው ወይስ በምንደኝነት? መቼም አቡነ ያዕቆብ ዲያቆኑ ባገለገበት ስፍራ ህዝቡ ይሁን ይደረግ እያለ በእልልታና በጭብጨባ ቅስና መስጠት እየቻሉ በሕገ ወጡ ሲኖዶስ እንዲሾም አይፈቅዱም። ስለሆነም ይህ ግለሰብ አውቆ ይሁን ሳያውቅ በጥራዝ ነጠቅነት የሚያደርጋቸውን አካሄዶች በጥንቃቄ መከታተሉ አግባብ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ የቤተክርስቲያናችንን አንድነት ይጠብቅልን።

ተክለጊዮርጊስ ዘ አትላንታ (አባል)